## ታገል—ለህልውና!

### በኢትዮጵያ ህዝብ ሁለንተናዊ ህይወት ላይ ያነጣጠረ የጥፋት ውሳኔን እንመክት!

የኢ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ፣ የድህነትና የኋላ ቀርነት፣ ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ የተንሰራፋ የሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት ጠበቃ የሆነውን የደርግ ስርዓት በብቃትና በፅናት በመታገል ያለፉት ትውልዶች መተኪያ የሌላት ውድ ህይወታቸው በመክፈል ስርዓቱን በመገርሰስ አገሪቱ ካስረከቡን በኋላ መታየት የጀመሩት መልካም የሚባሉ ውጤቶችን በፉከራና በቀረርቶ፣ በሽለላና በማስመሰል ሳይሆን በበዙ አለማየሁ አቶሙሳዎች መስዋእትነት የተገኙ ለመሆናቸው ፍፁም አያከራክርም፡፡

አሁንም አገራችን ወደ መካከለኛ ገቢ ለማሳደግ የተያዘው ራእይ ምንም ያህል አስቸጋሪና ውስብስብ ቢሆንም በቁርጠኝነትና በብቃት ታግሎ ከማሳካት ውጭ ሌላ አማራጭ እንደማይኖር ከእስከ አሁን ድረስ ያለው ተጨባጭ ሂደት መገንዘብ አያስቸግርም፡፡

በአሁኑ ወቅት በመንግስት በኩል እየታየ ያለው ቀስቃሽና ተስፋ ሰጪ መድረኮች ለህዝቦች ሙብትና ጥቅም ሲሉ የወደቁትን ሰማእታት አደራ አለማስቀጠል ከታሪክ ተጠያቂነት ማምለጥ የማይቻል መሆኑን በመገንዘብ ይበቃል! ሂንግአ! ይኾና ብለን በመነሳት ሰው መኖር እንዲችል ከችግር ተላቅቆ፣ መታገል አለበት ቅናቱን አጥብቆ እንዲሉ በየዘርፉ እየታዩ ያሉ ምዝበራዎች፣ የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባራት፣ የመልካም አስተዳደር ጉድፎች ወዘተ በፅናት መታገልና ማጋለጥ ያለብን መሆኑን አምነን እንቅስቃሴ ስንጀምር ወቅቱ በአለማችን ለ 27 ተኛ በአገራችን ደግሞ ለ 24 ተኛ ግዜ የአለም ኤድስ ቀን በምናከብርበት ወቅት ሆነን የአገር ጉዳይ፣ የህዳሴ ጉዳይ፣ የህዝብ ጉዳይ፣ የህልውና ጉዳይ የሆነውን የኤች አይ ቪ ኤድስ የቅድሚያ ትኩረት መስጠት እንዳለብን በመተማመን ነው፡፡

በአገራችን የኤድስ ቀን ስናከብር፡-

- ባለፉት ሳላሳ አመታት ኤች አይ ቪ ኤድስ ሁሉም የሕ/ሰብ ክፍሎች በተለይም አምራቹ ሃይላችንን በከፍተኛ ደረጃ የጎዳበትና ጉዳቱ ባላገመበት፣
- ዝምታ ይሰበር ብለን በተቀናጀና በተደራጀ አገባብ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ተጨባጭ ለውጥ ያስመዘገብንበት ግን በተገኘው ለውጥ ተኩራርተን ኤች አይ ቪ ኤድስ በተለመከተ ቃል እንዳንተነፍስ በአዋጅ የተከለከልን እስኪመስል ድረስ ዝምታ መርጠን ችግሩ እየተስፋፋ ባለበት፣
- ህይወት ከፍለን ያገኘናቸው ምርጥ የተግባር ልምዶችና ተሞክሮዎችን በመቀመር ሌሎች ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል፣ ተጎጂዎችን ለመንከባከብ ወደሚያስችል ደረጃ ለመሸጋገር ባልቻልንበት እንዲያውም የህዝቡን ጉዳት ሳያንገበግበን ከ 2300 በላይ ሰዎች በአንድ ጀንበር ኤች አይ ቪ አስመረመርን በማለት በድንቃድንቅ ማህደር (Genius book) ውስጥ ስምህን ለማካተት እንቅልፍ አጥተትነ እየሰራን ነው በማለት አንጀት መጣሽ የሆነውን ውሸታቸውን በቀረጠፉበት ወቅት (ደሮ ሲያታልልዋት በመጫኛ ጣልዋት እንዳሉ አበው)፣

በስመ አልጎሪዝም ክለሳ ሽፋን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የበላይ አመራሮች የብቃት ደረጃው እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን በጥናት ተረጋግጦ በአገልግሎት እንዳይውል ውድቅ የተደረገውን የኤች አይቪ መመርመሪያ ኪት ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ውሳኔ መስጠታቸው በእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍ የሆነበት ቀራና ወቅት እንገኛለን፣

በነገራችን ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ አህጉር ኤች አይ ቪ በተለያዩ ዙርያዎች ስለሚከሰት ለዚሁ ምርመራ አገልግሎት የሚውሉ የኤች አይ ቪ ኪቶች በአለም የጤና ጥበቃ ድርጅት የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ካገኙት ውስጥ የየአገራቱ የቆዳ ስፋት፣ የህዝብ ብዛትና የአየር ንብረት ግምት ውስጥ ባስገባ በተመረጡ ቦታዎች ሳይንሳዊ የመስክ ጥናታዊ ግምገማ በማካሄድ የኪቶች አይነትን በመምረጥ የብቃት ደረጃቸውን መሰረት ያደረገ የኪቶች የአጠቃቀም ቅደም ተከተል (ለመጀመሪያ ልየታ ምርመራ-screening test፣ ለማረጋገጫ ምርመራ-confirmatory test እና ለመጨረሻ ገላጋይ ምርመራ-tie breaker test) የሚውሉትን ኪቶች ይወሰናል፡፡

በመሆኑም በአገራችን እ.ኤ.አ በ 2004 የመጀመሪያው አልጎሪዝም ተዘጋጅቶ ስራ ላይ የዋለ ሲሆን ይህ መመሪያ እ.ኤ.አ በ 2007 ተከልሶ ተግባራዊ ሆኖዋል፡፡ አንድ አልጎሪዝም በአራት እስከ አምስት አመታት ግዜ ውስጥ መከለስ ስላለበት የ 2007 አልጎሪዝም ለሶስተኛ ግዜ ለመከለስ ህዳር 2005 ዓ.ም እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡

በዚህም መሰረት አልጎሪዝሙን ለመከለስ፡-

- ህዳር 2005 ዓ.ም፣ ታህሳስ 2005 ዓ.ም እንዲሁም የካቲት 2005 ዓ.ም ባደረጉት የደብዳቤና የጋዜጣ ጥሪዎች ኩባንያዎች የኪት ናሙናዎች በተደጋጋሚ እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡ የእንዳቸውም የግምገማ ውጤት ይፋ አልተደረገም (የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህ ተገፋ)፤
- የአልጎሪዝም ክለሳ አያስፈልግም በሚል ግንቦት 2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ኩባንያዎች ያቀረቡዋቸውን የኪት ናሙና እንዲሰበስቡ ተደርጓል፡፡ (ህግ እንደገና ተሰበረ)
- የአልጎሪዝም ክለሳ አስፈልጓል በማለት ታህሳስ 8 ቀን /2006 ዓ.ም በደብዳቤ በ 19 ቀናት ውስጥ፣ ታህሳስ 12 ቀን/ 2006 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በ 30 ቀናት ውስጥ፣ ታህሳስ 12 ቀን/2006 ዓ.ም በኢትዮጵያን ሄላርድ ጋዜጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የኪት ናሙና እንዲያቀርቡ ለኩባንያዎች የጥሪ ማስታወቂያዎች እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ (በመሰለኝና በደስአለኝ መንቀሳቀስ ይሉታል የኸው ነው)፣

በዚህ መልክ ባለጉዳዮችን ሲያጉላሉ ከርመው በእግር በፈረስ ተፈላጊ የሆነውን ኪት ለሕ/ሰቡ ነፍገው ምንም አይነት የላቦራቶሪ ሆነ የመስክ ጥናታዊ ግምገማ ሳያካሂዱ ታህሳስ 20 ቀን/2006 ዓ.ም የሚፈልጉዋቸውን ኪቶች በማካተት በአንድ ጀንበር ውስጥ አልጎሪዝሙን በመከለስ ታህሳስ 21 ቀን 2006 ዓ.ም ግዥ በዚሁ እንዲፈጸም ለመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ መመሪያ በማስተላለፍ የካቲት 2006 ዓ.ም የግዢ ሂደት ተጀምሯል፡፡ (የክህደት ውሳኔ የተሰጠበት ቀን)

ጉዳዩ የአገርና የህዝብ ጉዳይ መሆኑን አስቀድሞ የተረዳ ከኪት አቅራቢዎች አንዱ ድርጅት አቤቱታውን ለሚመለከተው አካል በማቅረቡ ግዢው ህግና ስርዓት ተከትሎ እንዲካሄድ የአልጎሪዝም ክለሳም በጥናት ላይ ተመስርተው እንዲከናወን ለጤና ጥበቃ ሚ/ር ሃላፊዎችን በመገለጹ መ/ቤቱ ቅዱስ ጳቅሎስ ሆስፒታል፣ ደብረ

ብርሃን ሆስፒታል እና ዱብቲ ሆስፒታል የመስክ ጥናት እንዲካሄድባቸው በመምረጥ ተጨማሪ ኪቶች ከኩባንያዎች እንዲቀርቡለት በማድረግ የ 11 ኪቶች የመስክ ጥናታዊ ግምገማ በማካሄድ የመጀመሪያ ሪፖርት ለውሳኔ ለበላይ ሃላፊዎች ቀርቧል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሃላፊዎች የሚፈልጉዋቸው ድርጅቶች ያገኙት የመስክ ጥናታዊ ግምገማ በጣም ዝቅተኛ ሆነ ስለተገኘ ስልጣናቸውን በመጠቀም በአጥኚዎች ላይ ጫና በመፍጠር ያላሟሉት ውጤት እንዳማሉ ተደርጎ ጥናቱ ተስተካክሎ ሪፖርቱ እንዲወጣ ማድረጋቸው ስለታወቀና አቤቱታ ለሚመለከተው አካል ቀርቦ ውሳኔው እንዲቀለበስ ተደርጓል፡፡ የሶስቱ ሆስፒታሎች የጥናት ውጤት ተደምሮ አማካይ ውጤቱ በመውሰድ ሪፖርቱ እንዲስተካከልና አልጎሪዝሙም ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ በሚመለከተው አካል ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሃላፊዎች የሚፈልጉዋቸው ድርጅቶች በደብረ ብርሃን ሆስፒታልና በዱብቲ ሆስፒታል ያገኙት ውጤት አነስተኛ ስለሆነና በጳውሎስ ሆስፒታል ግን የተሻለ ስለሆነ የሁለቱ ሆስፒታሎች ውጤት በመተው የጳውሎስ ሆስፒታል ውጤት ብቻ ነጥሎ በመውሰድና ሪፖርት በማዘጋጀት የኪት ናሙና ላቀረቡ ኩባንያዎች የግምገማ ውጤት ስለማሳወቅ በሚል ጥቅምት 19 ቀን/2007 ዓ.ም ውጤቱን ይፋ አድርጓል፡፡ በዚህ ላይ በመመስረትም ጨረታ አውጥተው ግዢ በማካሄድ ላይ እያሉ ለሚመለከተው አካል አቤቱታ ቀርቦ ይህንኑ ስለተረጋገጠ ጠበቅ ያለ የማስተካከያ መመሪያ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

- የተሰጣቸውን የመጨረሻ መመሪያ ግምት ያስገባ ይመስላል የሶስቱ ሆስፒታሎች ጥናታዊ ግምገማ አማካይ ውጤት በመውሰድ ለጥናት ከቀረቡት 11 ኪቶች አራቱ ብቻ በማሳለፍ ሰባቱን ውድቅ በማድረግ ዳግም በተስተካከለው ሪፖርት መሰረት የመጨረሻው ውጤት የኪት ናሙና ላቀረቡ ኩባንያዎች ጥር 22 ቀን/2007 ዓ.ም በድጋሚ ውጤታቸውን እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

  የጤና ጥበቃ ሚ/ር ለኤች አይ ቪ ምርመራ እና ለመጨረሻው ገላጋይ ምርመራ አገልግሎት የሚውሉ ኪቶችን በጥናቱ ውጤት መሰረት ግዥ የፈፀመ ሲሆን ቀሪው የግዥ በጀት ከ 95% በላይ የሚሸፍነውን ለመጀመሪያው ልየታ ምርመራ አገልግሎት የሚውለውን ኪት ግዥ ለመፈፀም ጥቅምት 9 ቀን /2008 ዓ.ም ጨረታ ሲያወጣ ሶስት ድርጅቶች የተሳተፉ ሲሆን በተካሄደው ጥናት የ sensitivity የብቃት ደረጃ በብቸኝነት 100% ያስመዘገበውና ባለፉት ሰባት አመታት ያለምንም የብቃት መጓደል በአገራችን ጥቅም ላይ የዋለውን እና በጨረታው የተሳተፈውን ኪት ውድቅ በማድረግ፡-

- የ sensitivity የብቃት ደረጃው እጅግ ዝቅተኛ የሆነውን ማለትም 98.28% የሆነውና አነስተኛ የሚባለውን የብቃት ደረጃ ≥99% መስፈርት የማያሟላ፣

- በአለም የጤና ጥበቃ ድርጅት የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ያላገኘና በቅርቡ ግዜ በወጣው የድርጅቱ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ፣

- ከፍተኛ የሆነ የናሙና ስርገት ችግር (sample absorption problem ) ያለበትና ሌሎች መሰረታዊ መስፈርቶችን የማያሟላ መሆኑን በጥናት የተረጋገጠ፣

- በተካሄደው አገር አቀፍ ጥናት የብቃት ደረጃው እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን በመረጋገጡ እጅግ ተፈላጊና መሰረታዊ መስፈርቶችን ስለማያሟላ ውድቅ የተደረገ መሆኑ ጥር 22 ቀን/ 2007 ዓ.ም በጽሁፍ ራሱ ጤና ጥበቃ ሚ/ር ማሳወቁ፣

- በኪቶች የአጠቃቀም ቅደም ተከተል መርህ አንፃር ለመጀመሪያው ልየታ ምርመራ አገልግሎት የሚውለው ኪት ከሌሎች የ sensitivity የብቃት ደረጃው የላቀ መሆን እንዳለበት የሚደነግገው እስታንዳርድ የማያሟላ፣

  ኪት መርጦ በጨረታው አሸናፊ ማድረጉ ያድናል ያሉት ኩል አይን አጠፋ እንዳሉ ሆነና የህዝቡን ጤና ይጠብቃል ያስጠብቃል ተብሎ እምነት የተጣለበት የተቋም አመራር፣

- በዘርፉ ከፍተኛ የሆነ የስነ ምግባርና የመልካም አስተዳደር እጦት ባለበት፣

- የጤና ግብአቶች እጥረት በከፍተኛ ደረጃ እየተባባሰ በሄደበትና ከ ሶስት አመት በፊት በአቅርቦቱ የለም የሚባል ጉዳይ የማይስተናገድበት ሁኔታ እንፈጥራለን በማለት ከነባራዊ ሁኔታው ውጪ ቃል ተገብቶ ቃል ኪዳኑ እንደጉም በኖ በቀረበት፣

- በስመ አልጎዚዝም ከለሳ ወጥ መመሪያ ጠፍቶ የግል አስመጪዎች ጭምር የኤች አይ ቪ መመርመሪያ ኪት ወደ አገር ውስጥ ማስገባት ባለመቻላቸው ሕ/ሰቡ የኤች አይ ቪ ምርመራ አገልግሎት ማግኘት ባልቻለበትና የብቃት ደረጃቸውን ባልተረጋገጡ ኪቶችና ኮንትሮባንዲስቶች ህገ ወጥ እንቅስቃሴ ለአደጋ በተጋለጠበት፣

- ከየትም ከየትም የሚለቃቀሙ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያልተገናዘቡ በተቋሙ የተነገሩ በርካታ ኢኒሼቲቮች ፍሬ ሳያፈሩ መና ሆነው በቀሩበት፣

- መንግስት የልማታችን፣ የህዳሴያችን የህልውናችን ካንሰር የሆነውን ኪራይ ሰብሳቢነትና የመልካም አስተዳደር እጦትን ፊት ለፊት ለመግጠም አምሮ በፅናትና በቁርጠኝነት ለመታገል የሚያስፈልግ ቅድመ ዝግጅት ባጠናቀቀበት ወቅት፣

  በአገሪቱ ህዝብ ጤና፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወት ከፍተኛ ቀውስ የሚያስከትልና ለእልቂት የሚዳርግ የብቃት ደረጃው እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን በጥናት ተረጋግጦ ውድቅ የተደረገውን ኪት ወደ አገር ውስጥ በማስገባት በአገልግሎት ላይ ለማዋል ያለምንም ከልካይ በስመ የፖለቲካ ውሳኔ የሚወስን አካል ሞት ሞት የሸተተው መሪ ካልሆነ በስተቀር በምንም መለኪያ ህዝባዊ አደራ የተቀበለ ሊሆን አይችልም፡፡ ለዚህ ይሆናል አበው ሲተርቱ መርዝ ይሆናል ብሎ ዳኛው ቢዘጋው፣ ሚኒስትሮች ከፍተው አስፈጁን ምነው፣ ያሉት

  እናም መሪዎቻችን ማን ይሆናል ይህንን የፃፈው ብላችሁ እንቅልፍ አጥታችሁ ከስራም ባዝናችሁ ከምትከርሙ ማንነታችንን እንንገራችሁ- በከፋፍለህ ግዛና በፈላጭ ቆራጭ የአመራር ዘይቤያችሁ ቀንበር ወድቀን ሮል ሞዴል

መሪን አጥተን ለአደርባይነት ተጋልጠን የቆየን አሁን ግን ለመራራው ትግል ተዘጋጅተን የተነሳን የአዲስቷ ኢትዮጵያ ተረካቢ የተቋማችሁ ወጣት ሰራተኞች ነን፡፡

ቅሬታ ማቅረብ የአጋርነት መገለጫ እንጂ ክስ አይደለም የሚለውን የመልካም አስተዳደር መርሆ የምትቀበሉ ከሆነ ለግዜው የሚከተሉት መለስተኛ ምከረ-ሃሳቦች እንለግሳችሁ፡-

<u>ምከረ-ሃሳቦች፡-</u>

1. **BATHO PELE--------PEOPLE FIRST**

   በፖለቲካና በአመራር ብቃታችሁ የተመሰከረላቸው ተብሎ ለሹመት የሚያበቃ ታሪክ ከፓርላማ ሲነገረን እውነትም የህዝብን መብትና ጥቅም ያከብራሉ፣ ያስከብራሉ ብለን በሙሉ ልብ እና እምነት ከሞርያም ምድር እንደመጣችሁ ነበር የተከተልናችሁ ግን ሃያሉ ተግባር ምስክር ነው እንዳሉ የብቃት ደረጃው እጅግ ዝቅተኛ የሆነን የኤች አይ ቪ መመርመሪያ ኪት ለማስገባት ለሶስት አመታት ያህል ፍፁም ለሰሚው የሚዘገንን ውሳኔ ወሰናችሁ፡፡ በሞርያም ምድር ሆድና ጭንቅላት ለየቅል ሆነና የጀኔሹን ሰውዬ ፍርፋሪ ለማግኘት ስትሉ ጸረ-ህዝብ የሆነውን ውሳኔ ለመወሰን መረጣችሁ፡፡ ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ እንዳሉ ሆነና፡፡

   የመረጣችሁት ኪት በጥቅም ላይ ማዋል ማለት ከ 10% በላይ False positive ወይም false negative ውጤት የሚያስከትልና የኢትዮጵያ ህዝብና መጪው ትውልድ ለከፍተኛ መቅዘፍት የሚዳርግ መሆኑን አማካሪዎቻችሁ ምክር አለመለገሳቸው ነገሩ የበለጠ እንቆቅልሽ አድርጎታል፡፡ ይህ ደግሞ ያየተመኛችሁትን ስም በድንቃ ድነቅ ማህደር የማኖር ህልም ቀርቶ ለዝንተ አለሙ በታሪክ ተጠያቂ በሚያደርጋችሁ የባንዳዎች ማህደር ውስጥ ስማችሁን ማኖር ይሆናል፡፡ አንመኝላችሁም

2. ከፖለቲካ **intoxication** እና **suffocation** ራስህን ማውጣት፣ የፖለቲካ ስልጣኑ የሉአላዊ ህዝባችን ስልጣን እንጂ የግለ ሰብ ገባሪ ፈጣሪ ስልጣን አለመሆኑ በመረዳት የተሰጠውን ሃላፊነት ህዝብን በአግባቡ ልናገለግልበት እንጂ የጥቅም ትስስር ልንፈጥርበትና ልንገለገልበት እንዳልሆነ ሁሉም በህግና በህግ ብቻ መወሰን፣

3. መድረኩ የህዳሴ ቅብብሎሽ እንጂ የውዳሴ ቅብብሎሽ አለመሆኑን መገንዘብ፣

   - የበፊቶቹ ዋልያዎች legacy ከሆነ ተጽእኖ እያሳደረብን ያለው ይህ fallacy መሆኑን በመረዳት ከዚሁ ራስህን ነፃ ማውጣት
   - ሌጋሲው የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አመለካከት፣ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ስነ ምግባር፣ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ተግባርና የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ እሴቶች ስጦታና ውርስ እንጂ የጥፋት ሌጋሲ አለመሆኑ

4. ዘርፍን መምራት በስሌት እንጂ በስሜት እንዳልሆነ መረዳት፣

በየኮንፈረንሱ እና በጽሁፍ ለሚሰጡ የኒዮ-ሊበራል አራማጆች ሃሳብ ሁሉም ለጤና ልማት ማስፈንጠሪያ ኢኒሸቲቮች ሊሆኑ እንደማይችሉ በመገንዘብ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ተፈላጊና መሰረታዊ የሆኑትን በመምረጥ መተግበር፣

5. የዘርፉ የበላይ ሃላፊዎችን ያሰባሰበው እስትሪንግ ኮሚቴ የጋሪዮሽ በሆኑት ወሳኝና አንገብጋቢ ጉዳዮች የሚስተዋሉ ችግሮች ከምንእዳዬ ወጥቶ ችግሮቹን ለመፍታት ዝምድናውን ፍቆ ለወገኑ ብሎ በመቆራረጥ መረባረብ

6. ሲቪል ሰርቫንቱ ከመሪዎች አሽከርነት ወደ የህግና የህዝብ አሽከርነት እንዲሸጋገር መፍቀድ፣ ሲቪል ሰርቫንቱ በየደረጃው ካሉት መሪዎች እየደረሰበት ያለውን ሁለንተናዊ ተፅእኖዎች ነጻ ካልወጣ የህዝብ አገልጋይ መሆን አይቻለውምና በተቋሙ የመልካም አስተዳደር መርሆዎችም በማስፈን ሰራተኛው የዚሁ ተጠቃሚ እና ተቋዳሽ መሆን የግድ ይላል፡፡ አመራሩም የዚሁ ቀያሽና ቀላሽ መሆን የግድ ይለዋል፡፡

7. በአህያ ቆርበት የተሰራ ቤት፣ መፍረሱ አይቀርም ጅብ የጨሆለት እንዲሉ ዘርፉ መጦሪያችንና ህይወታችን የተመሰረተበት ነውና በየደረጃው የሚታዩትን ችግሮች ሆድ ይፍጀው ብሎ ከመቀበል ይልቅ ያበጠው ይፈንዳ ነውና በትጋት ለመታገልና ለማጋለጥ እንቅስቃሴ መጀመር ከሁሉም ይጠበቃል፡፡

8. በሽተኞች ብሎ ሰው እንዳይሸሻችሁ፣ እባካችሁ ሰዎች አትተኙ ባልጋችሁ ነውና የተቋማችን የበላይ ሃላፊዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የፈፀማችሁዋቸውን ስህተቶች በማስተካከል ትክክለኛ አቅጣጫ በመከተል ሰራተኛውንና ህዝቡን ለመካስ ዝግጁ ከሆናችሁ እኛም የዘርፉ ባልደረቦች እኩል ዜጎች ነንና ለማገዝ ቁርጠኛ ሆነን እንገኛለን፡፡

ህገወጥነትን አንወርስም አናወርስም!

ለጤናችን አብረን እንስራ!

Amora

tagelamora@gmail.com